# የምሥራች

የምሥራች ደስ ይበለን (2)
የዓለም መድኃኒት ተወለደልን (2)

የምሥራች ደሰ ይበለን (2)
ጌታችን ተወልዶ አይተነው መጣን (2)

ንጉሥ ሄሮድስ ይህን ሲሰማ (2)
ፈልጋችሁ አምጡት በቀን በጨለማ (2)

አሸከሮቹም እንደታዘዙት (2)
በኮከብ ተመርተው ሕፃኑን አገኙት (2)

ሰገዱለት ከመሬት ወድቀው (2)

ወርቅና እጣኑን በረከቱን ሰጥተው (2)

## ንጉሥ ተወለደ

**ንጉሥ ተወለደ የዓለም መድኃኒት
መርገምን መለሳት ወደ ሥርየት
ሔዋንን አወጣት ከሲኦል እስራት
ባለ ግምጃ ጥላ ሆነች እመቤት**

***እሱ ባይወለድ መድኃኒታችን
እሱ ባይወለድ ቸሩ አባታችን
አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን***

**ሰላም ለእናንተ ይሁን በዚህ ላላችሁ
የክርስቶስን ቃል እንደሰማችሁ
የሕይወት ደስታ የተስፋ መሠረት
አንድነት ይስጣችሁ የሰው ልጆች አባት**

***እሱ ባይወለድ መድኃኒታችን . . .***

**ገና በሕፃንነት ሃይማኖት ሲመጀመር
አስደሳች ይሆናል ለኋለኛው ተግባር
በርቱና እናጥና ሃይማኖታችንን
ክርስቶስ ሰጥቶናል ዓለም አዲስን**

***እሱ ባይወለድ መድኃኒታችን. . .***

**በልጅነት ሰዓት ብዙ የደከመ
ዋጋውም ከፍ አለ እድሜውም ረዘመ
አይዟችሁ ወጣቶች እንሥራ በእድሜአችን
ክርስቶስ ሙቷል ለኃጢአታችን**

***እሱ ባይወለድ መድኃኒታችን
እሱ ባይወለድ ቸሩ አባታችን
አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን***

## እመቤታችን ላንቺ

እመቤታችን ላንቺ እናቀርባለን ምሥጋና
አንቺ የወለድሽው ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ሆኗልና (2)

ሕፃናት ስላወቁት ደግነትሽን በሙሉ
ወዳንቺ ሁልጊዜ ይማልዳሉ
ከፈጣሪሽ አማልጅን እያሉ (2)

## አምላክ መድኃኔዓለም

የሰው ነፃ አውጪ አምላክ
ከኃጢአት ቁራኛ አምላክ
በበረት ተወለደ አምላክ
ከእንሰሳት ጋራ አምላክ
*አምላክ (2) መድኃኔዓለም*

በበረት ሲተኛ አምላክ
ተጠቅልሎ በጨርቅ አምላክ
ሊያዩት ገሠገሡ አምላክ
ነገሥታት ከምስራቅ አምላክ
*አምላክ (2) መድኃኔዓለም*

ለኔ ብለው ሲሰግዱ አምላክ
የምሥራቅ ነገሥታት አምላክ
ከበው ያዩ ነበር አምላክ
የበረት እንሰሳት አምላክ
*አምላክ (2) መድኃኔዓለም*

ነገሥታት ሲሰግዱ አምላክ
እንሰሳት ካዩማ አምላክ
የአዳም ልጅ ያመስግን አምላክ
በጥዑመ ዜማ አምላክ

*አምላክ (2) መድኃኔዓለም*

# በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና

በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና በምድርም ለሰው ልጅ ሰላም (2X)
ተወልዷልና መድኃኔ ዓለም (2X)

የሞቱ ዘመን ማብቂያው ሲቃረብ
መቋጫው ሲደርስ አስፈሪው ወጀብ
ከድንግል ማርያም ጌታ ተወለደ
የጠብ ግድግዳ በክንዱ ተናደ

**አዝማች…**

ሰላም ታውጇል ነፃነት ሕይወት
ተወልዷልና የዓለም መድኃኒት
የሰማይ ዜማ ተሰማ በምድር
በአፈ መላእክት ለእግዚአብሔር

**አዝማች…**

ቃሉን አልረሳም የምሕረት ኪዳኑን
የማዳኑን ቀን ከአፉ የወጣውን
መሃለው ጽኑ ፀፀት የሌለበት
ለአዳነን አምላክ እልል እንበልለት

**አዝማች…**

አጽናኙን ድምጹን ሰማን በኤፍራታ
በዱር አየነው የፍጥረትን ጌታ
በሚቆምበት በሚያድርበት ሥፍራ
እንሰግዳለን በጽዮን ተራራ

**አዝማች…**

# ፍቅር አስገድዶት

ፍቅር አስገድዶት ጌታ ተሰዋልን
በደሙ አትሞ የራሱ አደረገን
ለሚደንቀው ፍቅሩ ምን ይከፈለዋል
ከበሮውን አንሱ ምሥጋና ይገባዋል } **አዝማች...**

(ምሥጋና ይገባዋል) በቤተልሔም ዋሻ (ምሥጋና ይገባዋል) ስለአየነው ፍቅር
«« የአምላክ ሰው መሆን «« ድንቅ ኃያል ምስጢር
«« ከሚያስፈራው ዙፋን «« በረትን ወደደ
«« ስለሰው ልጆች ሲል «« ክብሩን አዋረደ

**አዝማች...**

(ምሥጋና ይገባዋል) በአሕዛብ ምድር ላይ (ምሥጋና ይገባዋል) ሞገስ የሰጠኸን
«« በግብፅ ነገሥታት ላይ «« ታላቅ ያደረግከን
«« ያረገላችሁን «« ተዓምራቱን አውሩ
«« ለአማልክት አምላክ «« በእልልታ ዘምሩ

**አዝማች...**

(ምሥጋና ይገባዋል) ፍቅሩና ምኅረቱ (ምሥጋና ይገባዋል) በምን ቃል ይወራል
«« የመስቀል መከራ «« ከሞት ታድጎናል
«« ከዙፋኑ ወርዶ «« በበረት ያስተኛው
«« ሰዎች አመስግኑ «« ስለወደደን ነው

**አዝማች...**

# ማርያም ድንግል ንጽሕት

ማርያም ድንግል ንጽሕት ምልዕተ ፀጋ ደስ ይበልሽ (2X)
እመቤቴ እመቤቴ ፊትሽ ወድቄ ልሳለምሽ (2X) } **አዝማች...**

የቆምሽበትን አከብራለሁ በሥዕልሽ ፊት እሰግዳለሁ
ነፍሴ እንድትነፃ ከበደል ዘወትር ከፊትሽ እማልላለሁ
ግዞተኛ ነኝ በዓለም ነፃነቴ ነሽ ማርያም (2X)

**አዝማች...**

የሐሴቦን ልዑል ከሩቅ የጢሮስ ልጆች ከምሥራቅ
መጡ ገስግሰው በደስታ እናትነትሽን ለማድነቅ
አምኃ ይዤ ለክብርሽ እኔም ቆሜአለሁ ከደጅሽ (2X)

**አዝማች...**

አስጨናቂዎች ተሸንፈው ስለሚወድቁ ከጫማሽ
የታጠቁትን ሰይፍ ጥለው ማሪን አስምሪን የሚሉሽ
ልቤ ዘለለ በሀሴት ስምሽ ሲጠራ በጸሎት (2X)

**አዝማች...**

አጋንንት ፈሩ በሞገሷ ልታማልደን ስትነሳ
እፁብ ነው ፍቅሯ በረከቷ የዓለምን ፍቅር የሚያስረሳ
ስምሽ ይጠራል ለትውልድ ዘወትር ይኖራል ሲያማልድ (2X)

**አዝማች...**

# እልል እልል ደስ ይበለን

እልል እልል ደስ ይበለን
ወልድ ተወልዶ ነፃ ወጣን
ሰማይ ተከፍቶ ምስጢር አየን
} **አዝማች...**

የጥል መጋረጃ የተጋረደው
ከደመናት በላይ የተሰወረው
ግድግዳው ፈረሰ ድቅድቁ ተመታ
ከድንግል ሲወለድ የሠራዊት ጌታ

**አዝማች...**

በሥጋና በደም ሁሉን ተካፈለ
ፀና ዝምድናችን እኛንም መሰለ
በድንግል ማኅፀን ሆነ ተዋኅዶ
ተስፋው ተፈጸመ ክርስቶስ ተወልዶ

**አዝማች...**

የናፈቅነው መሲህ ሲገለጽ ማስያስ
ሕልማችን ሲፈታ ገነት ስትመለስ
ሰውና መላእክት በአንድ ላይ ዘመሩ
አስታርቆናልና ተዋርዶ ከክብሩ

**አዝማች...**

በሥጋና በደም ሁሉን ተካፈለ
ፀና ዝምድናችን እኛንም መሰለ
በድንግል ማኅፀን ሆነ ተዋኅዶ
ተስፋው ተፈጸመ ኢየሱስ ተወልዶ

**አዝማች...**

# ማርያም ደስ ይበልሽ

ማርያም ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ
በአንቺ ስላደረ የዓለም ሁሉ ጌታ

የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፎ ሲወጣ ብርሃን

መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሳሪ ገብርኤል ነበረ

ገብርኤል (2X) ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክን መወለድ ሥጋን በመልበስ

በቤተ መቅደስም ተቀምጣ ድንግል
ሐርና ወርቁን አስማምታ ስትፈትል

ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ስትሰማ
በእርሷ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ

እውነተኛው ንጉሥ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

## በጎል በጎል

**በጎል በጎል ሰብአ ሰገል በጎል ሰብአ ሰገል** (2)
**በጎል ሰብአ ሰገል ሰገዱለት** (2)

**ድንግል ማርያም ንጽሕት ቅድስት** (2)

**የጌታዬ እናት ምስጋና ይገባሻል**
**ከሴቶች ሁሉ ባንቺ አድሮብሻል** (2)

**ፀሐይ ፀሐይ ፀሐይ ሠረቀ** (2)
**ፀሐይ ሠረቀ ክርስቶስ ተጠምቀ** (2)

**በጎል በጎል አማኑኤል በጎል አማኑኤል** (2)

**እግዚአብሔር ፍቅሩን ሲገልጽልን**
**አንድያ ልጁን ለኛ ሰጠን** (2)

**እልል እልል ደስ ይበለን እልል ደስ ይበለን** (2)

**መድኅን ተወልዶ ነጻ አወጣ**
**ዮሐንስ አጥምቆ ድል አገኘን** (2)

**አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ** (2)
**የእግዚአብሔር ጸጋ ከላይ ወርዶብሽ**
**የዓለም መድኃኒት ተጠመቀብሽ** (2)

# ኦ! ክርስቶስ

ኦ! ክርስቶስ ኦ! አምላክ ብሩህ ነህ (2X)
ልቦናዬን አብራው በጥዑም ቃልህ (2X) } አዝማች

የታቦት ደመና (ክርስቶስ) የሲና ልምላሜ (ክርስቶስ)
ምነው ሙሴን በሆንኩ »» እንዳይህ ቀድሜ »»
የዮርዳኖስ ውኃ »» በላይህ ሲፈላ »»
ዮሐንስን በሆንኩ እንዳይህ በተድላ

አዝማች…

ነበልባል ሐመልማል (ክርስቶስ) ተዋኅዶ ሲና (ክርስቶስ)
ሙሴ በሩቅ ሆኖ »» ተመልክቷልና »»
በቀረበ ጊዜ »» ነገሩን ሊረዳ »»
ለእሥራኤል ሾምከው ሁሉ እንዳይጐዳ

አዝማች…

ሙሴ በበትሩ (ክርስቶስ) ኤርትራን ሲመታ (ክርስቶስ)
ተሻገሩ እሥራኤል »» በብዙ ደስታ »»
ይልታደሉቱማ »» የፈርዖን ሠራዊት »»
እየተሰጠሙ ቀሩ ወደ ኋሊት

አዝማች…

ትንቢቱ ጸደቀ (ክርስቶስ) የኢሣይያስ (ክርስቶስ)
ድንግልም ወለደች »» በመንፈስ ቅዱስ »»
ምነው ባደረገኝ »» እንደነ ሰሎሜ »»
ጌታዬ ሲወለድ ለማመስገን ቆሜ

አዝማች…

ሐዋርያት ሁሉ (ክርስቶስ) ዞረው ያስተማሩት (ክርስቶስ)
ወንጌልህ ብርሃን ነው »» ለዓለም መድኃኒት »»
ዮሐንስ እንዳለው »» ጥምቀተ ንስሐ »»
እታጠበዋለሁ የጐንህን ውኃ

አዝማች…

ሚካኤል በቀኝ (ክርስቶስ) ገብርኤል በግራ (ክርስቶስ)
ጥዑማን የሆኑት »» ሁሉም በየተራ »»
ሱራፌል ኪሩቤል »» ዓይናቸው የበዛ »»
ያመሰግኑሃል አንተን የዓለም ቤዛ

አዝማች…

# የዓለምን በደል

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ
ጽድቅን ለመፈጸም በደልን አጥፍቶ

የሠለሙ መሪ የሠላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ

የሰማዮች ሰማይ የማይችለው ንጉሥ
ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ
ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደ ፈረስ

ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሰርት
መጣ በደመና ሰማያዊው አባት
እየበሰከረ የልጁን ጌትነት

ባሕር ተጨነቀች ጠበባት በሬቱ
ዮርዳኖስም ሸሸ እልቆመም ከፊቱ
እንደ ተናረው ዳዊት በትንቢቱ

እንደ ምናነበው በወንጌል ተጽፎ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ
በርግብ ምሳሌ ክንፉን አሳርፎ

ባሕር ስትጨነቅ ተራራው ሲጨፍር
ሰማዩ ሲከፈት ደመናው ሲናገር
ዓለም በዛሬው ቀን አየች ይህን ምስጢር

# ሚካኤል አማላጅ ነው

በፍጡራንና ፈጣሪ መካከል
ድርሻ የተሰጠው ሰውን ለማገልገል
ተራዳእይ መልአክ ጠባቂ የእሥራኤል
የመላእክት አለቃ ስሙ ነው ሚካኤል

አማላጅ ነው ሚካኤል (2X)
የአምላክ ባለሟል
ለነሙሴ ለሕዝበ እሥራኤል } አዝማች...

ፈርኦን በእሥራኤል ላይ በትዕቢት ተነስቶ
ሲከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ
ይመራቸው ጀመር ሚካኤል በፋና
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና

አዝማች...

ሙሴ እንደታዘዘው አነሣ በትሩን
እጆቹን ዘረጋ ገሠጸው ባሕሩን
እንደ ግንብ ቆመ ባሕረ ኤርትራ
በደረቅ አለፉ እሥራኤል በተራ

አዝማች...

በአፎሚያ ላይ ሲፎክር ጠላት
ፈጥነህ የደረስከው ሊቀ መላእክት
እኛንም ጠብቀን ከክፋ መቅሰፍት
ፈጥነህ ድረስልን ሁነን ረዳት

አዝማች...

መልአኩ ሚካኤል አማላጃችን
እንለምንሃለን እንድትጠብቀን
አምላክ በፍርድ ቀን ፃድቃንን ሲጠራ
ዋስ ጠበቃ ሁነን ሚካኤል አደራ

አዝማች...

# ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር

ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል (2X)
መታመኛዬ እርሱ ነውና ይገባዋል ክብርና ምስጋና } **አዝማች...**

ፍቅሩን እያሰብን እንቅረብ ወደ እርሱ
ይምረናልና መሃሪ ነው እርሱ
በልባችን ይንገሥ ይግባ ከቤታችን
የሕይወታችን ዋልታ እርሱ ነው ተስፋችን (2X)

**አዝማች...**

ከቶ አላገኝም እርሱን የሚመስል
ነፍሴን የሚያከብራት የሚሰጠኝ ኃይል
በመከራ ሰዓት ከክፉ የሚያድነኝ
ከየት አገኛለሁ መጠጊያ የሚሆነኝ (2X)

**አዝማች...**

የለመለመ መስክ መሸሸጊያዬ ነው
በሰላም ወጥቼ ሰላም እገባለሁ
ተስፋዬ እርሱ ነው ይመራኛልና
ዘወትር አቀርባለሁ ክብርና ምስጋና
ዘወትር አቀርባለሁ ለአምላኬ ምስጋና

**አዝማች...**

እኔስ ይሻለኛል መቅረብ ወደ ጌታ
ጋሻዬ ነውና የነፍሴ አለኝታ
ስለዚህ እቀርባለሁ አልርቅም ከደጁ
ጠግቤ እኖራለሁ በበረከት እጁ (2X)

**አዝማች...**

# ሰላሜ በአንተ ነው

ሰላሜ በአንተ ነው የእኔ ጌታ
ዕረፍቴ በአንተ ነው የእኔ ጌታ
አልከለከል ምስጋና አልከለከል ውዳሴ ለአንተ ውለታ } **አዝማች...**

ጨለማዬ በአንተ በራልኝ
ከሰው ትከሻ ወረድኩኝ
የምመራበት ዱላዬ
በአንተ ተጥሏል ጌታዬ
አሁን በግላጭ አያለሁ
ሙሉ ሰው በአንተ ሆኛለሁ

**አዝማች...**

የመውገሪያው ድንጋይ ቀረልኝ
ጠላቴ በፊቴ አፈረልኝ
በፊትህ አቆምከኝ በፀጋ
ገዝተኸኛልና በዋጋ
ለውለታህማ ምን እላለሁ
ተመስገን ብዬ አልፈዋለሁ

**አዝማች...**

ሰላላው እጄን አቅንተሃል
ሽባነቴንም ተርትረሃል
ደካማነቴ ተወገደ
ያ ክፉ መንፈስ ተሰደደ
ታውጆልኛል ነፃነቴ
አመልክሃለሁ በሕይወቴ

**አዝማች...**

የዓይኔ ላይ ቅርፊት ወለቀ
ሸክሙ ከላዬ ወደቀ
በደማስቆ ብርሃን መታኸኝ
የራስህ ምርጥ ዕቃ አረግከኝ
ያ ከንቱ ድካሜ አለፈ
ልቤ ለፍቅርህ ተሸነፈ

**አዝማች...**

# የመስቀሉ ፍቅር

የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን (4X)
እመቤታችንን እናያታለን
የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው (4X)
እመቤታችን አለች ከጎናቸው

አባሕርያቆስ አባታችን
የመስቀሉ ነገር ቢገባው
ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር
ከእመቤቴ ጋራ ሲነጋገር
ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋገር

የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን (4X)
እመቤታችንን እናያታለን

ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ ቤዛዊት ዓለም
አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው (4X)

ተዋኅደ ስትል አማኑኤል አለችው አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው (2X)
ህሙማን ሲፈውስ ኢየሱስ አለችው አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው (2X)
ንጉሥ ነውም ብላ ክርስቶስ አለችው አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው (2X)
ተሰቅሎ ስታየው መድኅኑ አለችው አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው (2X)

ለመናኔው ጸሎት ልዩ ዕጣን
የዋሻው ሻማ ነሽ እመብርሃን
መዓዛሽ ሸተተኝ ከግሸን
ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን
ትርቢኝማለሽ ምን ልሁን

የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን (4X)
እመቤታችንን እናያታለን

ዳዊት በመዝሙሩ ያነሳሻል
የያዕቆብ ድንኳን ነሽ ይልሻል
የእግዚአብሔር ሀገር የሚሉሽ
እመቤቴ ማርያም አንቺ ነሽ (2X)

**ቤተልሔም ስሄድ አይሻለሁ**
**ቀራንዮ ስሄድ አይሻለሁ**
**ፍጹም አትለይም ከልጅሽ**
**የአንቺስ ልዩ ነው ፍቅርሽ** (2X)

**የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን** (4X)
**እመቤታችንን እናያታለን**

**ነይ ነይ እምዬ ማርያም**
**ነይ ነይ ቤዛዊት ዓለም**
**አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው** (4X)

**ተዋኀደ ስትል አማኑኤል አለችው** **አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው** (2X)
**ህሙማን ሲፈውስ ኢየሱስ አለችው** **አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው** (2X)
**ንጉሥ ነውም ብላ ክርስቶስ አለችው** **አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው** (2X)
**ተሰቅሎ ስታየው መድኀኑ አለችው** **አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችው** (2X)

# አንደበቴም ያውጣ

አንደበቴም ያውጣ የምስጋና ቅኔ
የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ በአይኔ
በገባኦን ሰማይ ፀሐይን ያቆመ
ዛሬም ጎበኝቶኛል እየደጋገመ
**አዝማች** (2X)

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከኃጢአት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ
የአናብስቱን አፍ በኃይሉ የዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኔ ጋ

**አዝማች**...

በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ
ከቅዱሳን ጋራ ስዘምር አብሬ
እርሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብትስቅብኝ
ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ

**አዝማች**...

አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድም
ለጣዖት እንድሰግድ ነገሥታት ቢቆጡም
ሁሉም ቢተውኝም ቢጠላኝም ዓለም
ጽናት ይሆነኛል ጌታ መድኃኔዓለም

**አዝማች**...

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከኃጢአት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ
የአናብስቱን አፍ በኃይሉ የዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኔ ጋ

**አዝማች**... (2X)

# ለማርያም

ለማርያም ለማርያም
እንዘምራለን ለዘለዓለም
እንዘምራለን ለዘለዓለም } **አዝማች...**

የተዘጋች በር (ለዘለዓለም) ሕዝቅኤል ብሏል (ለዘለዓለም)
ንጽህት ናት በእውነት »» በፍጹም ድንግል »»
አብነት አርገን »» እኛም እርሱን »»
<u>በፍጹም ፍቅር እንዘምራለን</u> (2X)

**አዝማች...**

የዋሂት እርግብ (ለዘለዓለም) ሰላም አብሳሪ (ለዘለዓለም)
ጨለማ ሕይወቴን »» ብርሃንን አብሪ »»
እማጸንሻለሁ »» ድንግል ለነፍሴ »»
<u>አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ</u> (2X)

**አዝማች...**

እጅግ የበዛ ነው (ለዘለዓለም) ያለኝ ፍቅር (ለዘለዓለም)
አይወሰንም »» አይነገርም »»
በእርሷ ደስ ይለኛል »» ሐሴት አደርጋለሁ »»
<u>ስሟን እየጠራሁ እዘምራለሁ</u> (2X)

**አዝማች...**

ነይ ነይ ስላት (ለዘለዓለም) ቀንና ሌሊት (ለዘለዓለም)
አትለየኝም »» ለኔ ቅርቤ ናት »»
ብፅዕት ብለው »» አመሰገኗት »»
<u>ክብሯን ሊገልጹ ቢያጥራቸው ቃላት</u> (2X)

**አዝማች...**

# ርሆቦት

ርሆቦት እያልን እንዘምር በእልልታ
ጌታ አብዝቶናል ውሎልናል ውለታ
የዝማሬ ነው የምስጋና ሰዓቱ
የእግዚአብሔር ልጆች ክንዳችሁን አበርቱ } አዝማች…

ቃኘተነዋል በገና መሰንቆውን
ላናቋርጥ በፊቱ ምስጋናውን
በእጣኑ ጢስ ታጅቧል ውዳሴያችን
ይሰማናል ያበዛን አምላካችን

አዝማች…

ለአገልግሎት ስንወጣ ጥቂት ነበርን
በረሃውን ስንጓዝ በዛ ዘመን
ለመለምን በፍቅሩ እንደ ዋርካ
ለዚህ ቀን አሰቦናል ጌታ ለካ

አዝማች…

ሁሉም ሆኗል በጊዜው በፈቃዱ
እንቅፋቱም ተነስቷል ከመንገዱ
ያነሳሳን ያበረታናል ገና
ዓለምን እንከድናለን በምስጋና

አዝማች…

ስናመሰግን ውለን እናድራለን
ያለድካም በፊቱ እንቆማለን
እንኳን በምድር በሰማይ በበጉ ፊት
ዝማሬያችን ይሰማል እንደ ዳዊት

አዝማች…